# ሀገረ-ሰባዊውን እውቀት መሠረት ያደረጉ ንዋየ ቅድሳት ፋይዳ እና ተግዳሮቶቹ

ፍሬህይወት ባዩ

## አጽኅሮተ ጽሁፍ[1]

በዚህ ጥናት ንዋየ ቅድሳት የተባሉት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ-ክርስቲያን(የኢ.ኦ.ተ.ቤ) የአምልኮ ሥርዓት የሚፈጸምባቸው እቃዎች ናቸው፡፡ እቃዎቹ ለአገልግሎት ከመዋላቸው በፊት የሚደረግላቸው የጸሎት ሥርዓትና የሚቀቡት ቅብዐ ቅዱስ ከመሰል ቁሶች ለይቷቸው ንዋየ ቅድሳት የሚለውን ስም አሰጥቷቸዋል። የጥናቱ ማእቀፍ የፎክሎር የጥናት መስክ ከሚያተኩርባቸው መካከል ቁሳዊ ባህል ላይ ያተኩራል። የኢ.ኦ.ተ.ቤ ንዋያተ ቅድሳት መካከል ሀገረ-ሰባዊ እውቀትን መሠረት ያደረጉ እንደሆኑ በማሳየት ለሀገር በቀል እውቀት ያላቸውን ፋይዳ ሊያሳጣቸው የሚችለውን ተግዳሮቶች መጠቆም የጥናቱ ዋና አላማ ነው። የጥናቱ አስፈላጊነት ንዋየ ቅድሳት ተግባራቸው ሃይማኖታዊ ቢሆንም ሀገረ-ሰባዊ እውቀትን መሰረት ያደረጉ መሆናቸው የተለያዩ ጠቀሜታዎች እንዳላቸው ያሳያል። አጥኚዋ ቀደም ሲል ንዋየ ቅድሳት ላይ ጥናት በማድረግ በየጊዜው የሚታይባቸውን ለውጦች በማስተዋል ከጊዜ ወደ ጊዜ ተግዳሮቶች መታየታቸው ተጨማሪ ጥናት ለማድረግ መነሻ ምክንያት ሆኗታል። በጥናቱ ውጤት ሀገረሰባዊውን እውቀት መሰረት አድርገው በመሰራት ላይ የሚገኙትን ለማሳያ ምሳሌ በማቅረብ እንደ ሀገር ሀብትነታቸው ያሉ ተግዳሮቶች ተጠቁመዋል። ንዋየ ቅድሳት የሚባሉት የኢ.ኦ.ተ.ቤ ለአምልኮ ተግባር የምትገለገልበት ሕንጻ ቤተ-ክርስቲያኑን ጨምሮ በህንጻ ቤተ-ክርስቲያን የውስጥ ክፍሎች ለአምልኮ ተግባር የሚያገለግሉ ናቸው። የኢ.ኦ.ተ.ቤ ንዋየ ቅድሳት በቀደሙት ዘመናት ሙሉ በሙሉ በሀገር ውስጥ ባለሙያ እና በአካባቢው በሚገኙ ቁሶች የሚሰራ ነበር። ከጊዜ ወደጊዜ የሚሰሩበት ጥሬ እቃ በከፊል ከውጭ ሀገራት በሚመጡ ጥሬ እቃዎች እየተተኩ እንዲሁም በውጭ ሀገራት ተሰርተው የሚመጡ ናቸው። ቁሶቹን የመስራት እውቀት በውጭ ሀገራት በሚገቡ ቁሶች እየተተኩ መሆን ከተግዳሮቶቹ ዋንኛው ነው። ይህ ተግዳሮት እንደ ሀገር ለዘመናት የኖረውን ሀገር በቀል እውቀት ማጣትን ያስከትላል። ጥሬ እቃዎቹንም ሆነ የተሰሩትን ከውጭ ሀገራት በማምጣት ባህላዊውንና ሀገር በቀሉን እውቀት ከማዘመን ይልቅ እንዲቀጭጭ አንዳንዶቹም ሙሉ በሙሉ እንዲጠፉ ምክንያትእየሆነ መጥቷል። በጥናቱ ለተነሱት ተግዳሮቶች እንደ መፍትሄ ሀሳብ የተጠቆመው የኢ.ኦ.ተ.ቤ ንዋየ ቅድሳትን ለመስራት የሚያስችል ትልቅ ኢንዱስትሪ ብታቋቁም ሃይማኖታዊ ደንቡን የጠበቁ ንዋየ ቅድሳትን ታገኛለች፣ ለምእመናኑ የስራ መስክ ትከፍታለች እንዲሁም ለባህል ኢንዱስትሪው ሀገረሰባዊው የእውቀት ሽግግር እንዳይገታ ትታደገዋለች።

[1] ባህልና ቱሪዝም ሚኒስተር ከወሎ ዩንቨርሲቲ ጋር ባዘጋጀው አውደ ጥናት ላይ ወሎ ዩንቨርሲቲ ግንቦት 24ቀን 2010ዓ ም መድረክ ላይ ቀርቦ ነበር።

## 1.መግቢያ

የዚህ ጥናት ትኩረት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን(የኢ.ኦ.ተ.ቤ) ለሃይማኖት ተግባር የምታውላቸውን ቁሶች ከሃይማኖታዊ ጠቀሜታቸው ጎን ለጎን ያላቸውን ሀገራዊ ፋይዳ የሚመለከት ነው። በኢ.ኦ.ተ.ቤ.ሥርዓት ቁሶቹ ሲሰሩ እንዴት እና ለምን እንደሚሰሩ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት አላቸው። የኢ.ኦ.ተ.ቤ መነሻ ሀሳቡን ከመጽሐፍ ቅዱስ ወስዳ ሀገረ-ሰባዊውን እውቀት መሠረት በማድረግ የተለያዩ ግለሰቦች ከአካባቢያቸው በሚያገኙት ጥሬ እቃ ለዘመናት ሲሰሩ ኖረዋል።

የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ አጥኚዋ ከዚህ ቀደም በተመሳሳይ ርእሰ ጉዳይ[2] ላይ ጥናት አካሂዳ ነበር። በዚህ ምክንያት ርእሰ ጉዳዩን በየጊዜው በመከታተል በተለይ ንዋየ ቅድሳቱ ላይ የሚታዩ ለውጦች "ሀገረሰባዊውን እውቀት እያቀጨጩ ነው" የሚለውን ስጋቷን በጥናት በመለየት የመፍትሄ ሀሳብ ለመጠቆም ከመነጨ ፍላጎት ነው፡፡ በተጨማሪም በአብያተ ክርስቲያናት እቃቤቶች ውስጥ ለብዙ ዘመናት የተቀመጡና ለብልሽት እየተዳረጉ ያሉ ንዋየቅድሳት በተሻለ ቦታ የሚቀመጡበት መንገድ እንዲመቻች ችግሮችን ለይቶ ማሳየቱ፣ "እቃዎቹን ከብልሽት ለመታደግ፣ የሀገርን እውቀት ለማስተዋወቅ እና ለቱሪስት መስህብ በመሆን ገቢ ማስገኘት ይችላሉ" የሚለው ሀሳብ ለጥናቱ መነሻ ምክንያት ሆኗል፡፡

የጥናቱ ዋና አላማ ሀገረ-ሰባዊ እውቀትን መሠረት ያደረጉ የኢ.ኦ.ተ.ቤ ንዋያተ ቅድሳት ምንነት በመጠቆም ለባህል ልማት ያላቸውን ፋይዳ እና ተግዳሮቶቹን ማሳየት ይሆናል። ዝርዝር አላማዎቹ፡-የንዋያተ ቅድሳትን ምንነት ማብራራት፤ ለባህል ልማት ያላቸውን ፋይዳ መጠቆም፤ የንዋየ ቅድሳቱ አሰራር እና ሰሪዎቹን በሚመለከት ያሉ ለውጦችን በተለይም ተግዳሮቶቹን ማሳየት ይሆናል።

የጥናቱ ጠቀሜታ ለኢ.ኦ.ተ.ቤ ንዋየ ቅድሳቱ አሰራር ሂደት ላይ ያሉትን ለውጦች እንድታስተውለው ይጠቅማታል። የንዋየ ቅድሳቱን አሰራር ሀገረሰባዊ እውቀት ትኩረት ተሰጥቶት እንደ አንድ የስራ መስክ ተወስዶ እንዲሰራበት መነሻ ሃሳብ ይጠቁማል። በቁስ ላይ ለሚሰሩ ተቋማት እንደ አንድ የስራ መስክ ታይቶ ሙያዊም ሆነ ሌሎች እገዛዎችን ለሚፈልጉ የቁሱ ሰሪ ግለሰቦች እገዛ ለማድረግ ያገለግላል። እንዲሁም እንደ አንድ የሀገር ሀብት ንዋየ ቅድሳቱ የሀገር መታወቂያ በመሆን ለሌሎች ሀገር ጎብኚዎች የአሰራር ጥበቡ ሀገራዊነቱ ላይ በማትኮር ለማስተዋወቅ ያግዛል። ከንዋየ ቅድሳት ጋር በተያያዘ ለሚያጠኑ ቀጣይ አጥኚዎች የመነሻ ሀሳብ በመስጠት ጠቀሜታ ይኖረዋል።

ለዚህ ጥናት በምልከታ እና በቃለ-መጠይቅ መረጃ ለማሰባሰብ ከአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ርዕሰ አድባራት እንጦጦ ማርያም እና ገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ-ክርቲያን ተመርጠዋል። የጥናቱ ዘዴ አሳሽና ገላጭ ዘዴዎች ናቸው፡፡ ምክንያቱም የንዋያተ ቅድሳቱን አሰራር፣ አጠቃቀምና

[2] "የኢትዮጵያ ኦርቶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ንዋየ ቅድሳት ሃይማኖታዊ እና ፎክሎራዊ ገጽታ፤ 2000።

አያያዝ ለማወቅ እነዚህ ዘዴዎች አማራጭ ሆነው ተገኝተዋል። የጥናቱ ቦታ አመራረጥ፤ የኢ.ኦ.ተ.ቤ የራሷ የሆነ ወጥ የአሰራር ሥርዓትና ትውፊት[3] ያላት ሲሆን ሃይማኖታዊ መመሪያዎቿ በሲኖዶስ የሚዘጋጁና ለሁሉም አጥቢያ አብያተ-ክርስቲያን የሚደርሱ ናቸው፡፡ በመሆኑም ንዋየ ቅድሳቱን በተመለከተ በሁሉም የኢ.ኦ.ተ.ቤ ተመሳሳይ ተግባር ላይ የሚውሉ ናቸው። የጥናቱን አላማ ለማሳካት ሁለት ቤተ-ክርስቲያን ማየት ተፈለገ እንጂ በመሠረቱ በይዘትም ይሁን በአፈፃፀም ደረጃ ሁለቱ ቤተ_ክርስቲያን የየራሳቸው የተለያየ አካሄድ የላቸውም፡፡

ለምርጫው የምቾት ናሞና እና የአላማ ናሞና አገልግሎት ላይ ውለዋል፡፡ በተለይም ሁለቱም ቤተ_ክርስቲያን ሙዝየም ያላቸው መሆኑ የኢላማ ናሙና ነው፡፡ አብያተ-ክርስቲያናቱን በቅርበት ማወቁና ተጠቃሚዎችን በቀላሉ ለማግኘት መፈለጉ የምቾት ናሙና ነው። በሁለቱም ቤተ_ክርስቲያን ከሚያገለግሉ ካህናት መካከል ሁለት ሁለት ካህን በአጠቃላይ አራት ቄሰ-ገበዞችና ሁለት ሊቃውንተ ቤተ-ክርስቲያን ለመረጃ አቀባይነት ተመርጠዋል። የተመረጡበት ምክንያት የንዋያተ ቅድሳቱ ጠባቂዎችና ኃላፊዎች እነርሱ በመሆናቸው በህልውናቸውና ጠቀሜታቸው ላይ የተሻለ እውቀትና ልምድ ይኖራቸዋል በሚል እሳቤ ነው፡፡ ለጥናቱ በቂና አስተማማኝ የሆነ መረጃ ለማግኘት ቃለ መጠይቅ፣ ምልከታና የሰነድ ምርመራ፤ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ጥቅም ላይ ውለዋል። በተጨማሪም በንዋያተ ቅድሳት ዙሪያ የተጠኑ ጥናቶች፣ የተጻፉ መጽሐፍትና ሌሎች ጽሑፎችን ሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጭ በመሆን አገልግለዋል።

## 2. ሀገረ-ሰባዊውን እውቀት መሠረት ያደረጉ ንዋየ ቅድሳት

### 2.1 የንዋየ ቅድሳት ምንነት

በቤተ-ክርስቲያን ግቢ /አጸድ/ ውስጥ ያለ ነገር ሁሉ በጥቅል ስሙ ንዋያተ ቅድሳት ይባላል፡፡ “ንዋይ ማለት ገንዘብ ማለት ነው፡፡ ቅዱስ ማለት ደግሞ የተለየ፣ የተከበረ፣ የተመረጠ ማለት ነው፡፡ ንዋየ ቅድሳት ማለትም በቤተ-ክርስቲያን የአምልኮ ሥርዓት የሚፈጸምባቸው የተቀደሱ እቃዎች ማለት ነው” (ኪዳነ ወልድ፣ 1948፡632)፡፡

እነዚህ ለሃይማኖት ተግባር የሚውሉ እቃዎች ንዋየ ቅድሳት የተባሉበት ምክንያት ለአገልግሎት ከመዋላቸው በፊት በሃይማኖቱ ሥርዓት መሠረት የሚደረግላቸው ጸሎት እና የሚቀቡት ቅብዐ ቅዱስ ነው። ለዚህም መነሻው መጽሐፍ ቅዱስ ሲሆን በብሉይ ኪዳን በመገናኛ ድንኳን በምስክሩ ታቦትና በዚያው የሚገኙት ንዋያት በተመለከተ የሚከተለውን ይላል፡፡

[3] ትውፊት ከጥንት ጀምሮ በቤተ-ክርስቲያን በኩል በቃል ሲነገር የመጣ። በቃልም በጽሑፍም ከአበው ወደ ትውልድ ሲተላለፍ የኖረና የሚኖር ማለት ነው፡፡ የሰው ልጅ እምነቱንና ሥርዓቱን ባህሉንና ታሪኩን በጽሑፍ ከመያዙ አስቀድሞ ከአዳም እስከ ሙሴ ቃል በቃል የተላለፉትን የእምነት፣ የሥርዓት፣ የትምህርትና የታሪክ ውርሶች እያጐላ ያቀርባል፡፡ መሠረታቸው ቅዱሳት መጻሐፍት ሆነው በትርጉም ያልተገለጡትን በተግባር ያሳያል፡፡ ትውፊት ከቅዱሳን መጻሐፍት ጋር የሚቃረን አይደለም (ነጋሽ፣ 1988፡35)፡፡

*የመገናኛውንም ድንኳን፣ የምስክሩንም ታቦት፣ ገበታውንም፣ [እ]ቃውንም ሁሉ፣ መቅረዙንም፣ የዕጣን መሠውያውንም፣ ለሚቃጠል መሥዋዕት የሚሆነውን መሠውያና [እ]ቃውን ሁሉ የመታጠቢያውን ሰንና መቀመጫውንም ትቀባበታለህ። ሁሉንም ትቀድሳቸ ዋለህ፣ ቅዱሳተ ቅዱሳንም ይሆናሉ፣ የሚነካቸውም ሁሉ ቅዱስ ይሆናል* (ዘፀ. 30፤26-30)፡፡

በሐዲስ ኪዳንም ይህንኑ መሠረት በማድረግ ንዋየ ቅድሳት የሚባሉት ቅብዐ ቅዱስ የተቀቡ ወይም በቅባት የከበሩ ንዋያት ናቸው፡፡ በቤተክርስቲያን በፊሊጺስዮስ[4] ከተመሠረተች በኋላ የክርስትና እምነት ተከታዮች ቁጥራቸው እየበዛ እንዲሁም የተለያዩ ሙያ ያላቸው ምእመናን የእምነቱ ተከታይ ሆኑ፡፡ እነሱም ለቤተ-ክርስቲያኗ የቤተክርስቲያን ምስጢራት መገለጫ የሆኑትን ልዩ ልዩ የቤተክርስቲያን መገልገያ እቃዎችን ሠሩ፡፡ "... *የቤተክርስቲያን ንዋያተ ቅድሳት ጻሕል፣ ጽንሐሕ፣ መስቀል እነሱንም የመሳሰሉት ሁሉ ተሠሩ*" (ሉሌ፣ 1986፤40)፡፡

*መጽሐፍ ቅዱሳዊ መመሪያ ተከትሎ ሀገረ-ሰባዊውን እውቀት መሠረት አድርጎ የተሰራ እቃ* በኢ.ኦ.ተ.ቤ ጸሎት ተደርጎ ቅባ ቅዱስ[5] በመቀባት ንዋየ ቅድሳት ይሆናል። ንዋያተ ቅድሳት እንዴት እንደሚሠሩ፣ ከምን እንደሚሰሩ፣ ለምን የያዙትን ቅርጽ እንደያዙ፣ ቀለማቸው ምሳሌያቸው በአገልግሎቱ ወቅት ማን መቼና እንዴት? መገልገል እንዳለበት፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊውን መሠረት በመያዝ ዝርዝር ሕግና ምሳሌያቸው ጭምር በጽሑፍ ሠፍሮ ይገኛል፡፡

ለምሳሌ የቤተ-ክርስቲያን አገልጋዮች በአገልግሎት ወቅት የሚለብሷቸው ልብሶች (አልባሳት ወይም ልብሰ ተክህኖ) የተለዩ እና የመልበሻ ጊዜውም የተወሰነ ነው፡፡ የልብሱ ዓይነት፣ አዘገጃጀቱ /አሰፋፉ/ መጠኑና ሌሎችም ተያያዥ ጉዳዮች የየራሳቸው ደንብ አላቸው፡፡ ንዋያተ ቅድሳቱ ለአገልግሎት ብቻ ተብለው የሚሠሩ ሳይሆን አሠራራቸው፣ የሚሰሩበት ጥሬ እቃ፣ መጠናቸው፣ ቅርፃቸው፣ የሚቀመጡበት አቀጣጫ፣ ብዛታቸው፣ ቀለማቸው፣ የሚገለገሉባቸው ግለሰቦች እና ሌሎቹም ሃይማኖታዊ ተምሳሌት እና ፍቺ አላቸው፡፡

የንዋየ ቅድሳቱን ዝርዝር ስንመለከት፤ ሕንጻ ቤተ-ክርስቲያኑ ጉልላትና ሻኩራዎች ጭምር። በአጸድ ውስጥ የሚገኙ ቤተ-ልሔም፣ ግብር-ቤት፣ ክርስትና-ቤት፣ ደወልና ሌሎችም። በሕንጻ ቤተ-ክርስቲያኑ ሶስት ክፍል (ቅድስት[6]፣ መቅደስ[7]ና ቅኔ ማሕሌት[8]) ከነመገልገያ ቁሶቹ ንዋያተ ቅድሳት

---

[4].*የጌታ ተከታይ የሆኑት ሐዋርያት ጳውሎስና በርናባስ በፊልጺስዮስ ገብተው ክርስትናን አስተማሩ ያስተማሯቸውና አሳምነው ያጠመቋቸውም ምእመናን /ክርስቲያኖች/ የተለየ ቤተ ጸሎት እንዲዘጋጅላቸው ባቀረቡት ጥያቄ መነሻ የመጀመሪያዋ ቤተ-ክርስቲያን በፊሊጺስዮስ እንድትታነጽ አድርጓል፡፡*

[5] ቅብዐ ቅዱስ - የተባረከ ቅባት በቤተክርስቲያን ለሥርዓተ ክርስትና መፈጸሚያ የሚያገለግል ከልዩ ልዩ ዕፅዋት ተቀምሞ የሚሠራ የሽቱ (የዘይት) ዓይነት፡፡

[6] *ሥጋ ወደሙን የሚቀበሉ ምእመናን፣ የሠርግ ሥነ ሥርዓታቸውን የሚፈጽሙ ሙሽሮችና ከቀዳስያን ውጪ ያሉ* ካህናት ተሰጥኦ በመቀበል ቆመው የሚያስቀድሱበት ክፍል ነው ማንኛውም ምእመን እዚህ መቆም አይችልም፡፡

[7] በብሉይ ኪዳን ቅድስተ ቅዱሳን በመባል የሚታወቅ ሲሆን ሦስት በሮች አሉት፡፡ በሦስቱም በሮች ላይ መጋረጃ እኩል ይጋረዳል፡፡ *መሥዋዕት የሚቀርብበት ታቦተ ሕጉ የሚቀመጠው በዚህ ክፍል ሲሆን ከካህናት በስተቀር ማንም* አይገባም፡፡ ካህናትም የሚገቡት ለአገልግሎት ብቻ ነው/የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን፣ 1994፡26/፡፡

[8]ወደ ቤተ-ክርስቲያን የውስጥ ክፍሎች ስንገባ የመጀመሪያው ክፍል ቅኔ ማኅሌት ይባላል፡፡

ናቸው። እነዚህም፤ በቅኔ ማሕሌት፡- ለመዝሙር አገልግሎት የሚውሉ ከበሮ፣ ጸናጽል፣ መቋምያ፣ ሥእል፣ መጻሕፍት፣ አትሮንስ፣ መቅረዝ እና መጋረጃ ይገኛሉ። ጥላ፣ ቃጭልና ሌሎችም በቅኔ ማሕሌትና በመቅደስ እየተዘዋወሩ አገልግሎት የሚሰጡ ናቸው። በመቅደስ አገልግሎት የሚሰጡ ንዋየ ቅድሳት በርካታ ናቸው። እነዚህም፡-ታቦት፣ ልብሰ ተክሓኖ፤ ዘውድ፣ መንበር፣ ጽዋዕ፣ እርፈመስቀል፣ ጻህል፣ ዐውድ፣ አጎበር፣ መነሳነስ(ጭራ)፣ መሶበ ወርቅ፣ ብርት፣ ሰን፣ ጽንሐሕ፣ ሙዳይ፣ መጎናጸፊያ፣ ቀጸላ፣ ቃጭል፣ መስቀል(የመጾር መስቀል)፣ ማህፈድ፣ ጥላና ሌሎችም ይገኙበታል። በተጨማሪም በተለያዩ አመታዊ ክብረ በዓላት ላይ ለአገልግሎት የሚውሉ ንዋየ ቅድሳት አሉ።

**2.2 የንዋያተ ቅድሳት ቁሳዊ ባህል ገጽታ**

ቁሳዊ ባህል በዐይን የሚታየውን በእጅ የሚዳሰሰውን፣ ከዘመናዊ ኢንዱስትሪ በፊት ጀምሮ የሰው ልጅ ፈጥሮ የተገለገለባቸውን ቁሳቁሶች፣ ቁሳቁሶቹ የተሠሩበትን ዘዴ ወይም ቴክኒክ፣ የልዩ ልዩ ምግቦችን አሠራር፣ የቅመም አቀማመም ብልኀትን፣ የልብስ፣ የቤት፣ የአጥር ወዘተ አሠራርን ሰዎች ልዩ ልዩ ሥራዎችን የሚያከናውኑባቸውን መሣሪያዎችና ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮችን ያጠናል፡፡ እቃውን እራሱን ማጥናት አንድ ዋና ተግባር ሲሆን አሠራሩን ማጥናት ደግሞ ሌላው ነው (ፈቃደ፣ 1991፡15)፡፡

በቁሳዊ ባህል የጥናት ዘርፍ ከሚጠኑት ቁሶች ሀገረ ሰባዊ እጅ ሥራ፣ ሀገረ ሰባዊ ሥዕል ሀገረ-ሰባዊ ምህንድስና፣ ሀገረ ሰባዊ ልብስ ይገኙበታል፡፡ የንዋየ ቅድሳትን ቁሳዊ ባህል ገጽታ ስንመለከት ትኩረታችን አሠራራቸው የሚሠሩበት ጥሬ እቃ ሀገረ-ሰባዊ መሆኑ ላይ ብቻ ይሆናል፡፡ ስለዚህ በቁሳዊ ባህል ሥር ከሚጠኑት ጉዳዮች አንዱ ለአምልኮ መፈጸምያ የሚውሉ እቃዎች፣ የማምለኪያው ቤት አሠራርና የሃይማኖቱ መሪዎች የሚለብሷቸው ልብሶች ይገኙበታል፡፡

ንዋየ ቅድሳቱ ከቁስነታቸው እና እንደማንኛውም እቃ ለአገልግሎት ከመዋላቸው ባሻገር በሃይማኖት ዐይን መታየት ይገባቸዋል፡፡ እነዚህ ቁሳዊ ሀብቶች የሚሰሩበት ቅርጽ እና የመሰራታቸው ምክንያት ሃይማኖታዊ ይዘቱን ይዞ በሀገረሰባዊው እውቀትና ቁስ የሚሰሩ ናቸው። ለምሳሌ አንድ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ንዋየ ቅድሳት ሲሆን የሚሰሩት ሰዎች ግን ያንን የሚመስል ማንኛውንም ቤት መስራት የሚችሉ የአካባቢው ባለሙያዎች ናቸው። ስለዚህ ሀገረሰባዊ እውቀት ከንዋየ ቅድሳቱ ጋር የሚያያዘው በሰሪው ጥበብ፣ በሚሰራበት ጥሬ እቃና እውቀቱ በሚሸጋገርበት ስልት ነው።

ሁሉንም መዘርዘር ሰፊ ስለሚሆንና አብዛኞቹ ሀገረ-ሰባዊ በሆነው አሠራር የተሠሩ ባለመሆናቸው ሙሉ በሙሉ ከዘመናዊ ኢንዱስትሪ ውጭ ከሚሠሩት አራቱም የቁሳዊ ባህል ዘርፎች መካከል ጥቂት ምሳሌ እንመለከታለን።

የዚህ ጥናት ትኩረት የሆኑት ንዋየ ቅድሳት ሀገረሰባዊ እጅ ስራን፣ ሀገረሰባዊ ስዕልን፣ ሀገረሰባዊ ምህንድስናን እና ሀገረሰባዊ ልብስን ያካትታሉ። በመጀመሪያ ከሀገረ ሰባዊ እጅ ሥራ መሶበ ወርቅእና ሙዳይ ለማሳያ ምሳሌነት እንመልከት። መሶበ ወርቅ አገልግሎቱ ዲያቆኑ ህብስቱን

ከቤተልሔም የሚያመጣበት ንዋየ ቅድሳት ነው፡፡ ሙዳይ ደግሞ ዕጣን የሚቀመጥበት ንዋየ ቅድሳት ሲሆን፣ የሚሰራበት ቁስ አክርማ (ስንደዶ) ነው፡፡ አክርማው ክረምት እንደወጣ መስከረም መጨረሻና ጥቅምት መጀመሪያ (እንደ አካባቢው ሊለያይ ይችላል) ይቀጫል ወይም ይለቀማል፡፡ ከተቀጨ በኋላ ከፊሉ መስፊያ የሚሆነው ይሰነጠቃል፡፡ ሰበዝ የሚሆነው ድፍን ይሆናል፡፡ ስንጥቁም ድፍኑም እንዲደርቅ አመቺ በሆነ ቦታ ይቀመጣል፡፡ በአብዛኛው በቤት ጣራ ላይ ታስሮ ይሰቀላል፡፡ የተሰነጠቀውም የተለያየ ቀለም እንዲኖረው ከተፈለገ ከዕፅዋት የተዘጋጀ ቀለም ውስጥ ይነከራል፡፡ ያልተነከረው ነጭ ወይም ሽሮ መልክ ይይዛል፡፡ ሲሰፋም ድፍኑ ከውስጥ ሆኖ ስንጥቁ ከላይ መስፊያ ይሆናል፡፡ መስፊያውን ለማስገባት ለሙብሻ የሚያገለግለው ወስፌ ይባላል፡፡ መያዣው የእንጨት ሆኖ ጫፉ የሾለ ቀጭን ብረት ነው፡፡ በአብዛኛው በሴቶች ይሰፋል፡፡ የሙዳይና የመሶበ-ወርቅ ልዩነታቸው የመጠንና የቅርጽ ነው እንጂ የሚሰሩበት ዘዴም ሆነ ጥሬ እቃው ተመሳሳይ ነው፡፡

ከሀገረ ሰባዊ ምህንድስና ሕንጻ ቤተ-ክርስቲያንን እንደምሳሌ እንውሰድ። ሦስት የቤተ-መቅደስ አሠራር ቅርጾች አሉ። እነዚህም፡- ክብ፣ ዋሻና ሰቀላማ እንደሆኑ ይገልጻል(ያሬድ፣ 1996፡47-50)። ነገር ግን የቤተ-ክርስቲያን የአሠራር ቅርጽን መወሰን እንደማይቻል ሲገልጹ፣ "በኢትዮጵያ ክርስትና ከገባበት ጊዜ ጀምሮ ልዩ ልዩ የአሠራር ቅርፅ ያላቸው አብያተ-ክርስቲያናት ሲታነጹ የቆዩ ቢሆንም ስለአጠቃላይ አሠራሩ ይህ ነው የሚባል የአሠራር ቅርፅ ለመኖሩ በቂ መረጃ ለማቅረብ ያዳግታል[9]፡፡ አብያተ-ክርስቲያናት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በቆርቆሮ (በግንብ) ከመሠራታቸው በፊት እንደተመሠረቱ የተሠሩት በሣር ክዳን፣ በእንጨት፣ ማያያዣቸውም ልጥ ሲሆን፣ ግድግዳውም አፈር(ጭቃ) ነበር፡፡ ሠሪዎቹም በአካባቢው ያሉ ምእምናን እንዲሁም ካህናት ናቸው። ዛሬም ድረስ እንጦጦ ማርያም ጊቢ ውስጥ በቆዳ መጫኛ ብቻ የተገናኘ ጣራና ግርግዳ ያለው ቤት ይገኛል፡፡

ሀገረ ሰባዊ ልብስን በተመለከተ ከንዋየ ቅድሳት መካከል ምሳሌ የሚሆኑ አሉ። ንዋየ ቅድሳት የሚሆኑ ልብሶች ካህናት እና ዲያቆናት በአገልግሎት ወቅት የሚለብሷቸው እንዲሁም ጳጳሳት የሚለብሷቸው ልብሶች ሀገረሰባዊውን መንገድ ተከትለው የሚሰሩ ነበሩ። ቀደም ሲል ካህናትና ዲያቆናት ይለብሷቸው የነበሩት ልብሰ ተክህኖም ከቆዳ፣ ከጥጥ የሚዘጋጁ ነበሩ፡፡ አሁንም ድረስ በቤተ-ክርስቲያን ዕቃ ቤት ውስጥ ይገኛሉ፡፡ ሆኖም አሁን ሙሉ በሙሉ በፋብሪካ በሚሰሩ የተለያዩ ጨርቆች የተተኩ ሲሆን አብዛኞቹም በሀገር ውስጥ ፋብሪካዎች የሚመረቱ ሳይሆኑ ከውጭ ሀገራት መጥተው እዚህ በሀገር ውስጥ የሚሰፉ ናቸው።

ሀገረ ሰባዊ ሥዕልን ምሳሌ እንውሰድ። በኢ.ኦ.ተ.ቤ ቀደም ሲል የሚታወቀው በስዕል አዋቂዎች የሚሳሉ የቅዱሳን ስዕላት ነበሩ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ከውጭ ሀገራት በወረቀት እና መሰል ቁሶች ላይ ተስለው የሚገቡ ስዕላት በርክተዋል። ሆኖም ሀገረ-ሰባዊው የቅዱሳን ስዕላት በሁሉም ቤተ-ክርስቲያን ባይሆንም ዛሬም በሕንጻ ቤተ-ክርስቲያን የውስጥ ግርግዳዎች እንዲሁም በጣራው የውስጠኛው ክፍል ላይ ይሳላሉ። እንዲሁም ጽሁፍ በወረቀት ላይ ከመሆኑ በፊት በብራና

[9] ምንጭ፣ ሊቀ ካህናት ከንፈ ገብርኤል አልታዬ(ቃለመጠይቅ)።

መጻህፍት ላይ ተስለው የሚገኙ የቅዱሳን ስዕሎች በርካታ ናቸው። በቤተ-ክርስቲያን የሚሳሉ የቅዱሳን ስዕላት የአሳሳል ደንብ አላቸው። ሥዕሉን ለመሳል የሚጠቀሙባቸው ቁሶች በአካባቢያቸው በቀላሉ ማግኘት ከሚችሉት ቁሶች እና ቀለማት ካላቸው እጽዋት ግብአት በመሆን ነው። እነዚህን ግብአት ለምሳሌ እንደሚከተለው ተጽፈው እናገኛለን።

ሥዕል ለመሣል ቀለም፣ ብሩሽ፣ ጨርቅ ማጣበቂያ ያስፈልጋል፡፡ የቀለማቱ ዓይነቶች የተለያዩ ናቸው። እንደ ቀለሞቹ ዓይነት የሚዘጋጁበት ጥሬ ዕቃ ይለያያል። ቀለማቱ እና የሚስሉበት ቁስ የብራና መጻሕፍት ለመጻፍ ከሚውሉት ጋር በአብዛኛው ይመሳሰላል፡፡ ብሩሽ ቀለማቱን ለመቀቢያ የሚያገለግል ነው። ሲሠራም በመጀመሪያ እንጨት ተጠርቦ ይሾላል፣ ከዚያም ከአህያ አንገት የተገኘ ጠጉር በክር የሾለው እንጨት ላይ ይታሰራል፡፡ በቁልቋል ደም ይጣበቃል፣ የአህያው ጸጉርም እንዳይፈታ ያደርገዋል፣ ይህም ብሩሽ ሆኖ ይሳልበታል፡፡ በለሴ ጨርቅ (ነጭ ቀለም የሚቀባ ለሥዕል መሣያ የሚያገለግል ጨርቅ) ነው፡፡ ጨርቁም ከጥጥ በፈታይ አማካይነት ተዘጋጅቶ፣ በሸማኔ የሚሰራ ነው፡፡ ግርግዳውና ጨርቁ የሚጣበቅበት ማጣበቂያ በቤት ውስጥ የሚዘጋጅ ነው። ይሄውም የቀይ ጤፍ ወይም የስንዴ ዱቄት በውሃ ቀጠን ብሎ ይበጠበጥና በእሳት ላይ ተጥዶ ይፈላል፡፡ የፈላው ሲበርድ ግርግዳውና ጨርቁ ተቀብቶ ይጣበቃል፡፡ ሙጫ ለብራና ሥዕል አንድም ለሐረግ ቀለማት መበጥበጫና ወዝ መስጫ ያገለግላል፡፡ የግራር ሙጫ ከውሃ ደባልቆ በጸሀይ ወይም በእሳት ቀልጦ ለብራና ሥዕል ከቀለማት ጋር ይደባለቃል፡፡ የቁርበት ማሸጊያ ከእንቁላል ጋር ተደባልቆ ለቀለማት መበጥበጫና ማድረቂያ የሚሆን ነው፡፡ ዝግጅቱም የከብት ቆዳ በደንብ ታጥቦ ይተለተላል። የተተለተለውም በሸክላ ይቀቀላል፡፡ በደንብ ሲነፍር (ሲበስል)በማጣሪያ ይጣራል፡፡ የተጣራው ውሃ በዕቃ ተደርጐ በቀዝቃዛ ቦታ ይቀመጣል፡፡ የተቀመጠውም ይረጋል፡፡ በደንብ ከረጋ በኋላ ይያያዛል፡፡ የተያያዘው በቢላዋ ተከፋፍሎ ሳንቃ ላይ ተደርጐ ይደርቃል፡፡ ለሥራ በተፈለገ ጊዜ በሚያስፈልገው መጠን እየተበጠበጠ ይሠራበታል፡፡ አገልግሎቱ የሥዕሉን ጨርቅ ግድግዳ ላይ ለመለጠፍ ከስንዴው ሙቅ ጋር ተደባልቆ መለጠፊያ ይሆናል፡፡ በተጨማሪም ለቀለም መሥሪያ (ለዓይነት) ይጠቅማል፡፡ የዕንቧይ ውሃ የተለያዩ ነፍሳት ቀለሙን እንዳይበሉት ለመከላከል ከቀለማት ጋር ይደባለቃል፡፡ ከሥዕል ጋር ተያይዞ ሙያዊ ስያሜ ተሰጥቶታል፡፡ ለምሳሌ ናዞርድ የቀለም ስም ሲሆን፣ ሰማያዊ ማለት ነው፡፡ ነጠብጣብ- ጌጣጌጥ ማለት ነው፡፡ ለሂ- ማለት ውበት መስጠት ማለት ነው። ከአንገት በላይ የሚያሳይ ሥዕልን ጉርድ ይሉታል፡፡ እያንዳንዱን የሚያሳየውን አካል የሚያሳይ ከሆነ ማዋዛት ሲሉት መሥራት ወይም መሣል ለማለት ደግሞ ሐረግ መጣል ይሉታል፡፡ የብርሃንን አቅጣጫ ተከትሎ የሥዕሎችን ክብነት የሚያሣይ ሥዕል ከሆነ ብሩህና ጥላ ይባላል፡፡ ሥዕል ያላረፈበት ትርፍ ሰሌዳ ካለ ደግሞ መዳብ ይባላል (ሀብተ ማርያም፣ 1963፡268-271)፡፡

ሥዕሉ ሲሳል የጌታ ስቅለት፣ የቅዱሳን፣ የመላእክት እየተባለ አቅጣጫቸው የቀለሙ አመራረጥና ሌሎችም ተያያዥ ጉዳዮች ትኩረትና ጥንቃቄ ተሰጥቷቸው ነው፡፡ ስዕሉን ከመሳል ባሻገር ተምሳሌቶች ለስዕሉ የሚያስፈልጉ ቅመማዎች ወደ ሌላም እውቀት የሚሸጋገሩ ናቸው። ስለዚህ የስዕል መሳል ጥበቡ ሲጠና የተለያዩ እውቀቶች አብረው እንደሚጠኑ ለመገመት ከባድ አይሆንም።

እንደ ስዕሉ ሁሉ ሌሎችም ንዋየ ቅድሳት በአካባቢው ከሚገኙ ጥሬ እቃዎች በቀላሉ የሚሰሩ ነበሩ። ከእነዚህ መካከል የመስቀል ስራ አንዱ ሲሆን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከውጭ ሀገራት ተገዝተው በሚገቡ የመስቀል አይነቶች በሀገር ውስጥ መሰራታቸው ሙሉ በሙሉ ባይቀሩም እየተለወጡ ይገኛሉ። በቅኔ ማህሌት ከሚያገለግሉ ንዋየ ቅድሳት መካከል በተለይ ምእመናን በስጦታ መልክ የሚሰጧቸው መቋሚያዎች ልክ እንደ ስዕል እና መስቀል በከፊል ከውጭ የሚመጡ ሲሆን እነዚህም በአብዛኛው በትልልቅ አድባራት የሚገኙ ናቸው። ሌሎችም በተመሳሳይ መልኩ በአካባቢው ባሉ ቁሶች ያለ ዘመናዊ ኢንዱስትሪ የሚሰሩ ነበሩ፣ ዛሬም ድረስ የሚሠሩ ለምሳሌ እንደ ከበሮ ያሉ አሉ። ሌሎቹ ንዋየ ቅድሳት የሚታይባቸው ለውጥ ንዋየ ቅድሳቱ የሚሰሩበት ጥሬ እቃ ከውጭ ሀገራት መጥተው ሀገር ውስጥ ባሉ ባለሙያዎች ይዘጋጃሉ። ለምሳሌ ልብሰ ተክህኖ እና ዣን ጥላ ተጠቃሽ ናቸው። በአጠቃላይ ከላይ የተመለከትናቸው ቁሶች አሰራር ቀደም ሲል ሙሉ በሙሉ ኢትዮጵያ ውስጥ ከዘመናዊ ኢንዱስትሪ ውጭ የሚሰሩ ነበሩ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በነባራዊው እውቀት ላይ መጨመር በጥቂቱም ቢሆን የሚታይ ሲሆን በአብዛኛው ግን ከውጭ በሚመጡ ጥሬ እቃዎች መሰራታቸው እየተለመደ መጥቷል።

**2.3 የንዋያተ ቅድሳት ተለዋዋጭነት ባሕርይ**

በንዋየ ቅድሳት አሠራር ትርጉምና ምሳሌ ላይ የሚታዩት ለውጦች በየዘመኑ የሰው ልጅ የሚፈጥራቸው አዳዲስ ግኝቶችና ፈጠራዎች አስተዋፅዎ አላቸው፡፡ ለረዥም ዘመን ሲያገለግሉ የነበሩ ንዋየ ቅድሳት በሌላ እየተተኩ መምጣት፡፡ የሃይማኖት ተቋሙ ለሚተኩት አዳዲስ ቁሶች ሃይማኖታዊ ፍቺ አለመስጠት ይታያል፡፡ ለምሳሌ ዛሬ በስም ብቻ የሚታወቁ፣ አገልግሎታቸው ግን በሌላ የተተኩ ንዋየ ቅድሳት ዐብይ ፍትህ አወቅ በ1963ዓ.ም ከሠራው ዲማፅ ላይ የሚገኙትን ለምሳሌ እንመልከት፡፡

ሰቀላማ፡- ወደ ላይ ከፍ የተደረገ፣ የተንጠለጠለ/ አራት መዓዘን ቅርጽ ያለው ቤት ሆኖ ጐኑ ረዘም ያለ ከንፋማ የሆነ። ይህ ጥንት ከኢትዮጵያ ቤተ-ክርስቲያን ሕንጻ አሠራር አንዱ ነበር፡፡ ዛሬ ግን አልፎ አልፎ ቢገኝ እንጂ ቀርቷል(11)፡፡

ርካም፡- እምነበረድ ነጭ ድንጊያ ገልባጣ ጻሕል ቁርባነ ኅብስት የሚቀመጥበት ዛሬ በሌላ ተተክቶ ስሙም እየተረሳ ነው (11)።

አያሚን(ያሚን)ወይም ኰከም ፡- የፍም የእሳት መጫሪያ ዲያቆኑ የሚገለገልበት ዛሬ መጫሪያ በሚል ተተክቷል /27/፡፡

እብሪቅ(ኩስኩስት)፡- ጉጠት ያለው ማንቆርቆሪያ መሰል ነበር። ማንቆርቆሪያ ተብሏል።

ማይዕቃ፡- በቤተልሔም ለውሃ መያዣ የሚያገለግል ከሸክላ የተሠራ እንስራ ነው። ዛሬ በፕላስቲክ ባልዲ ወይም በጀሪካን ተተክተዋል (41)፡፡

ቅብዐ መንግሥት፡- (ቀበዐ፣ ለቀለቀ) መሰየሚያ፣ መሾሚያ፣ ለክብር የሚደረግ ከእፅዋት የሚቀመም የሥርዓተ ንግሥ መፈጸሚያ፣ የክብርና ማዕረግ ማሳያ ነው፡፡ የሚቀመመው ከቀረፋ፣ ከበለስ፣ ከከርቤና ከወይራ ሲሆን ዛሬ ንግሥና ስለሌለ አይዘጋጅም(47)፡፡

ቀንአት፡- ከዕጣን ዕንጨት የሚቀመም ሽቱ ከአረብ ሀገር የሚበቅል ለቤተ-ክርስቲያን አገልግሎት ሲውል የነበረ፤ እንዲሁ ተመሳሳይ አገልግሎት የነበረው ጠርቤንቶስ (ቴሬቤንቶስ)የሚባል ሽቱ ነበር ዛሬ ግን የለም (49)።

ሙዳየ እፍረት፡- በፈረ፣ ቀባ፣ ለቀለቀ፣ ለቤተ ክርስቲያን የሚያገለግል ሽቱ ማስቀመጫ ነበር (52)፡፡ ዛሬ ሽቶው በፈሳሽ መልክ እንጂ በዱቄት (በእጣን) መልክ አይታወቅም። እንደ ሽቱ የሚያገለግለው በዕጣን መልክ መጥቶ ጨሶ እንፋሎቱ ነበር። ዛሬ በቤተ-ክርስቲያንም ሆነ በሌላ ቦታ የለም።

በትረሐዲን፡- ክብር የተሠራ ዱላ ካህናት የሚይዙት (59)። ዛሬ ከብር የተሠራ የለም፣ ስሙም አይታወቅም።

በትረ ወርቅ፡- ከወርቅ የሚሠራ በትር ከፍ ያለ ሥልጣን ያላቸው የቤተ ክህነት ሰዎች የሚይዙት (62)።

መንበረ መንግሥት፡- ንጉሡ ሲነግሡ ለክብር የሚጥ የንጉሥ መቀመጫ ወይም ዙፋን ማለት ነው(63)።

ሉል፡- የክብር ድንጋይ ነገሥታት በእጃቸው የሚይዙት ክብ ሆኖ በላዩ ላይ መስቀል ያለበት በእንቁላል (በሎሚ) ቅርፅ የሚሰራ (64)።

ዘመናዊነቱ የፈጠራቸው አዳዲስ ነገሮች በፊት በቤተ_ክርስቲያኗ የማይታወቁ፣ የማይደረጉ ቀኖናውም ያላወቃቸው ታቦት ማንሻ፣ ታቦት ማክበሪያ የሚባሉ ለክብረ በዓል ታቦት የሚሸከመው ካህን የሚገለገልበት ነው[10]፡፡ ሌላው ባለሕግ ቄሶች እንደመነኮሣት የሚለብሱት ቀሚስና በአናታቸው የሚደፉት ነው፡፡ ጳጳሳት በተለያዩ ቤተ ክርስቲያን ለአገልግሎት ሲሄዱ የሚቀድሱት በልብሳቸው ነበር፤ ዛሬ ግን ጳጳሳት መቀደሻ ልብስ ይዘው ነው፡፡ እነዚህ እስከአሁን ሕግ ያልወጣላቸው በመሆናቸው ምናልባት እየተለመዱ ሲሄዱ ቀኖናው ይወጣ ይሆናል፡፡ መለመዳቸው ግን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቷል፡፡

በዘማናት ጥበቡን እያራቀቀች ከሃይማኖታዊ ተግባራቸው ባሻገር የሰው ልጆችን ቀልብ የሚስቡ እና ለሌላም መስከ የሚተርፍ እውቀት ባለቤቶች እንዲሆኑ ንዋየ ቅድሳቱ ጥልቅ ድርሻ አላቸው። ስለዚህ ሃይማኖቱ ለባህሉ እንዲሁም ለእድገት የሚሆነውን እውቀት ለመውሰድ በቅድሚያ በሃይማኖታዊ ቁሶች ላይ የሚታዩትን ለውጦች በመመልከት ከሃይማኖት ተቋሙ እና ሌላም የሚመለከተው አካል በለውጦች ውስጥ ያሉትን አሉታዊ መልኮች ለመለየት እና መፍትሄ ለመሻት

---

[10] ምንጭ መምህር ፍስሐጽዮንን(ቃለመጠይቅ)።

ተግዳሮቶቹን መመልከት ተገቢ ይሆናል። በንዋየ ቅድሳቱ ሀገረ-ሰባዊ እውቀት ላይ ያሉ ተግዳሮቶችን ለማሳያ እንደሚከተለው ቀርቡዋል።

## 3. ተግዳሮቶች

በንዋየ ቅድሳቱ አሰራር ላይ በየዘመኑ ለውጦች አሉ። ለውጡ በሚሰጡት አገልግሎት ሳይሆን የአሰራሩ መለያየት እና በተለይ ሀገረ-ሰባዊ የነበረው የአሰራር ዘዴ መቅረት ነው። የቀረበት ምክንያት በውጭ ሀገራት ልምድ ላይ በመመስረት የሕንጻ አሰራር አይነቱን መለወጥ። ሀገር ውስጥ ይሰሩ የነበሩትን ከውጭ ሀገር በሚመጡት መተካት። ቀደም ሲል በተለያየ የከበሩ ማእድናት ይሰሩ የነበሩ እና አገልግሎት ያቆሙትን በተገቢው ቦታ ሳይቀመጡ መቅረት። ከእነዚህ ጋር ለሌላውም የቁሳዊ ባህል ልምድ እውቀት ሽግግር ያገለግሉ የነበሩት አብረው መቅረት ይገኙበታል። እነዚህ ተግዳሮቶች በጥቂት ንዋየ ቅድሳት ማሳያነት እንደሚከተለው እንመልከት።

ተክህኖ ልብስን በተመለከተ ከቀኖናው የወጣ ስለመሆኑ ለዚህ ጥናት ምልከታ ሲደረግ በተደጋጋሚ ታይተዋል። በጽሑፎች ከሰፈሩ ማስረጃዎች ለምሳሌ "በግዢ በመባዕና በሥዕለት መልክ ወደ ቤተ-ክርስቲያን የገቡ የአንዳንድ ልውካን ልብስ አሰፋፍና ቀለሞቻቸው በየጊዜው እየተለዋወጡ ነው፡፡ ካህናቱ ሲቀድሱ በራሶቻቸው ላይ የሚቀዳጃቿዋቸው ኩፋሎች የምዕራቡን ቲያራ መስለው ያስደነግጣሉ" (ሐመር፣ ሐምሌና ነሐሴ፣ 1994፡13)፡፡ በማለት ከጊዜ ወደጊዜ ከቀኖናው የወጡትን የልውካን ልብሶች ይገልጿቸዋል፡፡ ቀደም ሲል ቤተ-ክርስቲያኗ ትገለገልበት የነበረውን በሀገር በቀሉ እውቀት የተሰራውን ልብስ በየዘመኑ ምቹ እንዲሆኑ ባለሙያዎቹን እያበረታታች እና ስራዬ ብላ በመከታተል እውቀቱ ቢዳብር ባለሙያው ቢበዛ ዛሬ ሙሉ በሙሉ ከውጭ የሚመጡትን ልብሶች ብቻ ለንዋየ ቅድሳት አናውለውም ነበር።

ሕንጻ ቤተ-ክርስቲያን የውስጥና የውጭ ቅርጽ (አሠራር) "ሕንጻ ሲታነጽ ምስጢር እንዳይፋለስ፣ አሠራሩ ትርጉም አልባ እንዳይሆን አበው ይጠነቀቁበታል፣ ቅርጹ ከክርስቶስ የዓለም ቤዛነት ጉዞ፣ ከቅዱሳን መላእክት አገልግሎትና ተጋድሎ ጋር እንዲያያዝ ሆኖ ነው" (ያሬድ፣ 1996፣47)፡፡ የተሠሩት ሕንጻዎች ይህን ጠብቀዋል ወይ? ስንል "አሁንማ የሚሠራው ቤተ-ክርስቲያን የሚመስለው ምኩራብ እንጂ ቤተ-ክርስቲያን አይደለም፡፡ ግን ካቴድራል ይሉታል በማለት ካህናቱ ይመልሳሉ"[11]።

በዚህ ዘመን በሚታነጽ ሕንጻ ቤተ-ክርስቲያን ለማንኛውም ተመልካች ማየት እንደሚቻለው ቀድሞ የነበራቸውን ቅርጽም ሆነ የሚሰሩበትን ጥሬ እቃ ሙሉ በሙሉ ተቀይሯል። ሃይማኖታዊ ተምሳሌት የነበራቸው ከቤተ-ክርስቲያኑ አሰራር ጋር እንዲቀጥሉ ያልተደረጉ ምሳሌዎች አብረው ቀርተዋል። ለምሳሌ አሁን በሚሰሩት ሕንጻ ቤተ-ክርስቲያን ላይ ቦታ የሌላውን ጉልላት፣ ሻኩራ እና በጉልላቱ ላይ የሰጎን እንቁላል ወይም የሰጎን እንቁላል ቅርጽ ነበረ።

[11] ምንጭ መምህር ፍስሐ ጽዮን(ቃለመጠይቅ)።

ከብ የሆነው እና ጉልላት የነበረው የሕንጻ ቤተ-ክርስቲያን ቅርጽ ሲቀር ሀገር በቀሉን እውቀት ተከተለው የሚሰሩ ባለሙያዎች እውቀት ጭምር አብረው ጠፍተዋል። ዘመናዊውን የሕንጻ አሰራር ጥበብ የተማሩት ሲመጡ ባህላዊው እውቀት ለዘመናዊው መሰረት ሳይሆን ቀርቷል። ምናልባት ባለሙያዎች ህይወት ላይ ጥናት ቢደረግ ሙያው መተዳደሪያቸው ከነበረ ስራ ፈተዋል ወይም እንደዋዛ ለዘመናት ያቆዩትን እውቀት ይዘውት አልፈዋል።

ሌላው ተግዳሮት አገልግሎት ያቆሙ ንዋየ ቅድሳት አቀማመጥ ምቹ ያለመሆን ነው። አገልግሎት ሲሰጡ ቆይተው ሲያረጁ በእቃ ቤት ውስጥ ይቀመጣሉ። እቃቤት ግን አገልግሎት ያቆሙት ብቻ ሳይሆን አገልግሎት የሚሰጡ ሆነው ትርፍ ንዋየ ቅድሳት በተለይም ለአመታዊ ክብረ በአል ብቻ የሚፈለጉት የሚቀመጡበትም ነው። አገልግሎት መስጠት ያቆሙ ንዋየ ቅድሳት ለእቃዎቹ አቀማመጥ አመቺ ባልሆነ ቦታ መቀመጣቸው በቀላሉ ለብልሽት ይዳረጋሉ። አገልግሎት መስጠት ያቆሙ ንዋየ ቅድሳት በትልልቅ አድባራት እና እቃ ቤት ባላቸው አብያተ-ክርስቲያናት እንጂ በተለይ በገጠር ያሉ አብያተ ክርስቲያናት እቃ ቤትም የላቸው። ስለዚህ እነዚህ ንዋየ ቅድሳት ገበዝ ሆኖ በሚያገለግለው ካህን ቤት ይቀመጣሉ፡፡ በእቃ ቤት የሚቀመጡበት ቦታ፣ አቀማመጣቸው እና የሚቀመጡበት ቤት ለረዥም ጊዜ ሳይከፈት መቆየት ጠባብ መሆን በአጠቃላይ ምቹ ባለመሆኑ በቀላሉ ለብልሽትና ለጥፋት ይዳረጋሉ።

ንዋየ ቅድሳት በኢ.ኦ.ተ.ቤ ቀኖና መሠረት፣ መሠራት ያለባቸው በቤተ-ክርስቲያኗ ነው። ማንኛውም ሰው መሥራት ስለሚችል ብቻ አይሠራቸውም[12]። ዛሬ በገበያ ላይ የሚገኙ ንዋየ ቅድሳትን ማን ይሰራቸዋል? ብለን ስንጠይቅ የሚሠራው በቀኖናው ቤተ_ክርስቲያኗ እንድታሰራ ያዛል። በተግባር ግን በቤተ-ክርስቲያን ሳይሆን በነጋዴ ይሰራል፡፡"[13] ይህን ለማረጋገጥ የንዋየ ቅድሳት መሸጫ ሱቆችን እና ማስታወቂያቸውን መመልከት ብቻ በቂ ነው፡፡ ለዚህ እንደዋነኛ ምክንያት የሚነሳው የቁሶቹ ከውጭ ሀገራት መምጣት በአምጪዎቹ እና ገዝተው ለቤተ-ክርስቲያን በስጦታ በሚሰጡ ግለሰቦች አመለካከት "ዘመናዊነት(የተሻለ ንዋየ ቅድሳት ከውጭ ሀገራት የሚመጣው ነው) ከውጭ ማምጣት ነው" ብሎ ማሰብ የሚጠቀስ ነው። ለዚህ እንደ ምሳሌ በቤተ-ክርስቲያን ደጃፍ "ከኢየሩሳሌም የመጡ ንዋየ ቅድሳት" የሚለው ማስታወቂያ የተለመደ ሆኗል። ሌላም ምክንያት ሆኖ የሚነሳው የቁሶቹ አምጪ እና ሻጭ ንዋየ ቅድሳቱ ሃይማኖታዊ ይዘት(ምናልባትም የሃይማኖቱ ተከታይ ላይሆን ይችላል) የሌላቸው መሆኑ እና ሀገረሰባዊው እውቀት መጥፋቱ ጉዳዩ አይሆንም።

በአጠቃላይ ተግዳሮቱን ለማስቀረት ዋናው መታየት የሚገባው ነጥብ ለእውቀት መሰረቱ ባህል ወይም ሃይማኖት ብቻ አይደለም፤ አንዱ ከሌላው ይወስዳል በሂደት እየተደጋገፈ፣ እየተወራረሰ አንዱ ሌላውን ያበለጽጋል። በተለይም የኢ.ኦ.ተ.ቤ እንደማንኛውም የክርስትና ሃይማኖት መሠረቷ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ሆኖም በርካታ ኢትዮጵያዊ መልኮች ይታዩባታል። ንዋየ ቅድስቱን ከሕንጻ ቤተክርስቲያን ጀምራ ስትሰራ ልክ እንደመጽሐፍ ቅዱሱ ሁሉ ንዋየ ቅድሳቱን እንደተሰሩ ከሌላው ዓለም አልተቀበለችም። የተጻፈውን የሃይማኖት መሰረት ይዛ በአካባቢው ከሚገኙ ባለሙያዎች

[12] ምንጭ፣ ሊቀ ካህናት ክንፈ ገብርኤል አልታዬ(ቃለመጠይቅ)።

[13] ምንጭ፣ ሊቀ ካህናት ክንፈ ገብርኤል አልታዬ(ቃለመጠይቅ)።

እና በቅርብ ከሚገኙ ጥሬ እቃዎች ሰራች። በባህሉም ሆነ በሃይማኖት እውቀት ውስጥ ያሉት የአንድ ሀገር ህዝቦች ናቸው። ስለዚህ ንዋየ ቅድሳት ውስጥ የምናየው የአሰራር ጥበብ የህዝብ እውቀት የሀገር መታወቂያም ነው። ኢትዮጵያ ከምትታወቅባቸው ቅርሶቿ የኢ.ኦ.ተ.ቤ ንዋየ ቅድሳት አንዱ ነው። ለምሳሌ የቅዱስ ላሊበላ ህንጻ ቤተ-ክርስቲያን። በተለይም የቀደመው ዘመን አሻራዎች ሆነው ከዚህኛው ዘመን በበለጠ እውቀት የነበረበት የተለየ ጠቢባን ህዝቦች እንደነበሯት ከሚያሳዩት አሻራዎች ንዋየ ቅድሳት ተጠቃሽ ናቸው።

## 4.ተግዳሮቶቹን ለመቋቋም የተሰሩ ቀደምት ስራዎች

ከተግዳሮቶቹ መካከል አንዱ በአብያተ ክርስቲያናት እቃቤቶች አገልግሎት የማይሰጡ ንዋየ ቅድሳት አያያዝ ነበር። ይህን ተግዳሮት መከላከል ከጀመሩት መካከል ለጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያ ቦታ የነበሩት ሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት እንደ ማሳያ ምሳሌ የሚጠቀሱ ናቸው። እነዚህም በገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን እና ርእሰ አድባራት እንጦጦ ማርያም ቤተ-ክርስቲያን ቅጥር ግቢ ውስጥ  የሚገኙ ሙዝየሞች ናቸው። ሙዝየሞቹ አገልግሎት መስጠት ያቆሙ ንዋየ ቅድሳት እና የነገስታት አልባሳት እንዲሁም ስጦታዎችን የያዙ ናቸው። በሁለቱም ሙዝየሞች ውስጥ የሚነበኙት ቅርሶች በአብዛኛው ንዋየ ቅድሳት የነበሩ ናቸው።

በገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ-ክርስቲያን የሚገኘው ሙዝየም፤ በገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ-ክርስቲያን ቅጥር ግቢ ውስጥ የሚገኘው ሙዝየም በሙዝየም መልክ የተደራጀው በሰበካ ጉባዔው አስተባባሪነት ነው፡፡ የተመረቀው ሚያዝያ 21 ቀን 1982 ዓ.ም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሪዎስ ፓትሪያሪክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ነው፡፡ ሙዝየም የሆነውም የቀድሞው ደወል ቤት ሲሆን ደወል ቤቱን ያሠሩት ንግሥተ ነገሥት ዘውዲቱ እና አፄ ምኒልክ ናቸው፡፡ ንግስቷ የካቲት 4/1909 ዓ.ም ቅብዐ መንግሥት ተቀብተው ዘውድ ሲደፉ ሥርዓተ ንግሡ የተፈጸመበት በዚህ ደወል ቤት ውስጥ ነበር። የሙዝየሙ ውስጣዊ አሠራርም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አሠራርን የተከተለ ሆኖ ዘመናዊ በሆነ መልኩ የተሠራ ነው፡፡

በሙዝየሙ ውስጥ የሚገኙ ቅርሶችም፣ ልብሰ ተክህኖ፣ የሥርዓተ ቅዳሴ ንዋየ ቅድሳት፣ መስቀሎች፣ ከተለያዩ ነገስታትና ግለሰቦች የተሰጡ የወርቅ እና የብር መስቀሎች፣ ካባዎች፣ መጐናጸፊያ፣ ድባብ፣ ጥላ፣ የሥርዓተ ቅዳሴ አልባሳት፣ አክሊሎች፣ ጽና፣ ከሩሲያ መንግሥት ለቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን የተሰጠ ደወልና ሌሎችም ንዋያተ ቅድሳት አሉ። እንዲሁም የነገሥታት መገልገያ ቁሳቁሶች፣ የተለያዩ ፎቶዎችና ሌሎችም ቅርሶች በሙዝየሙ ውስጥ ይገኛሉ።

በርእሰ አድባራት እንጦጦ ማርያም ቤተ-ክርስቲያን የሚገኘው ሙዝየም፤ በርእሰ አድባራት እንጦጦ ማርያም ቤተ-ክርስቲያን ሙዝየሙን ለመሥራት በ1975 ዓ.ም መሠረት ተጣለ፡፡ በ1979ዓ.ም ኅዳር 13 ቀን ተመርቆ ሥራ ጀመረ፡፡ መርቀው የከፈቱትም ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩት ፍቅረ ሥላሴ ወግደረስ ናቸው፡፡ ሙዝየሙ እንዲሠራ ሐሳብ ያቀረበው የቤተ-ክርስቲያኑ አስተዳደር ሲሆን ያሰራው የባህል ሚኒስቴር ከጠቅላይ ቤተ ክህነትና ከርእሰ አድባራት እንጦጦ

ማርያም ቤተክርስቲያን ሲሆን ወጪውን የሸፈኑት ሁለቱ ተቋማት ናቸው፡፡ አሁን በአገልግሎት ላይ የሚገኘው ሙዝየም ሙሉ በሙሉ በቤተ-ክርስቲያኗ ሥር ይተዳደራል፡፡

በሙዝየሙ የሚገኙት ቅርሶች ቀድሞ በቤተ-ክርስቲያኗ እቃ ቤት ይቀመጡ የነበሩ ናቸው፡፡ ሙዝየሙ ክፍሉ ጠባብ ስለሆነ እቃ ቤት ውስጥ የሚገኙት ንዋየ ቅሳት ሙሉ በሙሉ አልወጡም። የቀሩት እቃ ቤት ሊቀመጡ ግድ ሆኗል፡፡ በሙዝየም ውስጥ ያሉ ቅርሶችም በአብዛኛው ለአጼ ምኒልክ ከተለያዩ ሀገራት የተሰጡ ስጦታዎች፣ አፄ ምኒልክ፣ ንግሥት ዘውዲቱና ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ለቤተክርስቲያኗ ያበረከቱት ንብረቶች፣ እቴጌ ጣይቱ እንዲሁም አፄ ምኒልክ ለአድዋ ጦርነት ሲዘምቱ የያዟቸው የጦር መሣሪያ፣ የተለያዩ እቃዎች፣ ልብሳቸው፣ ነጋሪት እና ሌሎችም አሉ፡፡ የቤተ ክርስቲያን መገልገያ የነበሩ ንዋያተ ቅድሳት መካከል ሥዕል፣ የልኡካን ልብስ፣ የዜማ መሣሪያዎች፣ ፅና፣ ፀናፅል፣ ማኅፈዳት፣ ድባብ፣ ጥላ፣ የብራና መጻሕፍት፣ መቅረዝ፣ ፅዋ፣ ዕርፈ መስቀል፣ መሶበ ወርቅ፣ እጣን ማቅረቢያ፣ መስቀሎችእና የብራና መጻህፍት ሲሆኑ አብዛኞቹም የተሠሩት ከወርቅና ከብር ነው፡፡

## 5.ንዋየ ቅድሳት የትኞቹን ያካትታሉ?

ንዋየ ቅድሳት የትኞቹን ያካትታሉ? የትኞቹንስ አያካትቱም? ለሚለው በተለይ የነገሥታት መገልገያ የነበሩና ለቤተ-ክርስቲያን የተሰጡ እንዲሁም በአብያተ-ክርስቲያናት ሙዝየም ውስጥ የሚገኙትን አንዳንዶቹ "ንዋየ ቅድሳት ናቸው" ሲሉ፤ ሌሎቹ ደግሞ "ንዋየ ቅድሳት አይደሉም" በማለት በቅርስነት ብቻ ይፈርጇዋቸዋል፡፡ ለምሳሌ እንጦጦ ማርያም ሙዝየም ውስጥ ያሉ የነገሥታት መገልገያ የነበሩና ለነገሥታቱ የተለያዩ ሰዎች በስጦታ ያበረከቷቸውን ዕቃዎች በቤተ-ክርስቲያን ቅጽር ግቢ ውስጥ መገኘታቸው ንዋየ ቅድሳት ያሰኛቸዋል በሚል ከንዋየ ቅድሳት የሚመድቧቸው አሉ[14]።

ከነዚህ መካከል በሙዝየሙ ውስጥ የሚገኙት የነገሥታት ልብስ፣ የጦር መሣሪያ እንዲሁም የተለያዩ መገልገያዎች ናቸው፡፡ እንዲሁም ዐብይ ንዋየ ቅድሳት በማለት በትረ መንግሥት፣ መንበረ መንግሥት፣ ሎል (እንቁ)፣ ነገሥታት በእጃቸው የሚይዙት፣ አክሊለ መንግሥት፣ አክሊለ ወርቅ፣ ዘውድ (1963፣ 59-67) በማለት ዘርዝሯቸዋል፡፡ የነገሥታት መገልገያ ንዋየ ቅድሳት አይደሉም የሚሉት ደግሞ፡- "የነገሥታት ልብስ፣ ዘውዶችን እና መሰል መገልገያዎች ቅርስ እንጂ ንዋየ ቅድሳት አይባሉም፡፡ የንጉሥ ዘውድም የወግ ዕቃ እንዲሁም ቅርስ ነው። ንዋየ ቅድሳት የሚባለው የፓትሪያርኩ ልብስ፣ ዘውድ፣ የጳጳሳት ቆቦች፣ የካህናት፣ የዲያቆናቱ ለአምልኮ ተግባር ሲሰማሩ የሚለብሷቸው ልብሶች ናቸው።

እነዚህ ዝርዝሮች ንዋየ ቅድሳት ሆኑም አልሆኑ አሁን ባሉበት ሁኔታ ግን የሀገሪቱን የተወሰነ ዘመን ማሳያ አሻራዎች ናቸው። ከዚያም በላይ "ንዋየ ቅድሳቱ" የሚገኙበት ቦታ ሙዝየም በመሆኑ ማንኛውም መንብኘት የፈለገ አካል ለመንብኘት ወደ ሙዝየሙ ሲሄድ ገንዘብ ይከፍላል። ስለዚህ

---

[14] ምንጭ፣ ሊቀ ካህናት ክንፈ ገብርኤል አልታዬ(ቃለመጠይቅ)።

ሙዝየሙን ለሚያስተዳድረው አካልም ሆነ ለአስጎብኚዎቹ በአጠቃላይ ለሀገር የስራ መስክ በመሆን ገንዘብ ያስገኛል።

በአጠቃላይ የጥናቱ አብይ ትኩረት የኢ.ኦ.ተ.ቤ ሃይማኖታዊ መሠረቱን ሳይለቅ ቁሱ እንዲሰራ የራሷን ግዴታ ብትወጣ፤ ለሀገር የሚተርፍ እውቀት፣ ገንዘብ፣ የሀገር መታወቂያ ታተርፋለች። ንዋየ ቅድስቱ ለኢ.ኦ.ተ.ቤ ወሳኝ እና ቤተክርስቲያኗ እስካለች ሁሌ የሚሰራ ነው። ቤተ-ክርስቲያኗ ንዋየ ቅድሳቱን የምትፈልጋቸው ለአምልኮ ሥርዓት መፈጸሚያ እንጂ ሀገረሰባዊው እውቀት ፈጠራ እና መዳበር ዋና ጉዳዩዋ ስለሆነ አይደለም። ስለዚህ ሀገር በቀሉ እውቀት በሃይማኖት ሰበብም ሆነ በሌላ ምክንያት መኖሩ መዳበሩ የተለያዩ ጠቀሜታዎች አሉት።

## 6.ማጠቃለያ እና ይሁንታ

ንዋየ ቅድሳት የምንላቸው በጥቅሉ ከሕንጻ ቤተክርስቲያኑ ጀምሮ መገልገያ ቁሶቹን በሙሉ ነው። አሰራራቸውን ስንመለከት መነሻው መጽሐፍ ቅዱስ ይሁን እንጂ የአሰራሩን መመሪያ አንብበው በተግባር የሚሰሩት የሃይማኖቱ ተከታዮች ወይም ጥበቡ ያለቸው ግለሰቦች ናቸው። የሚሰራባቸው ጥሬ እቃም በአብዛኛው በዚሁ በሀገራችን የሚገኝ ነው። ለጥናቱ መረጃ የተሰበሰበባቸው ርእሰ አድባራት እንጦጦ ማርያም እና ገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ሙዝየም ውስጥ በቅርስነት ተቀምጠዋል። ቀደም ሲል በኢትዮጵያ የነበረው የንግስና ሥርዓቱ ከኢ.ኦ.ተ.ቤ የተያያዘ ስለነበረ ለነገስታት የተሰጡ ስጦታዎችና የንግስና ልብሶች እንደ ንዋየ ቅድሳት በሙዝየም ውስጥ ቅርስ ሆነው ይጎበኛሉ።

የንዋየ ቅድሳቱን ሀገረሰባዊ መሆን በተለይ ከቁሳዊ ባህልነታቸው ጋር በማያያዝ ስንመለከት አብዛኞቹ በሀገር በቀሉ እውቀት የተሰሩ ናቸው። ከፊሎቹ ግን በለውጥ ላይ የሚገኙ ናቸው። ለውጡም ሀገር በቀሉ እውቀት በውጭ ሀገር ጥሬ እቃና የአሰራር እውቀት እየተተካ መምጣት ነው። ለሀገር በቀሉ እውቀት መዳበር መሆን ይገባው የነበረው የሀገር በቀሉን እውቀት ወደ ውጭ ሀገራት መላክና ማስተዋወቅ ነበር። ሆኖም በተቃራኒው ሀገር በቀል የነበሩትን ምርቶች በውጭው መተካት ሆኗል።

የሀገርበቀሉ እውቀት በውጭ የመተካት ሂደት ከምክንያቶቹ አንዱ የኢ.ኦ.ተ.ቤ በቀኖናው መሠረት የራሷ ንዋየ ቅድሳት ማምረቻ እና መከፋፈያ ሊኖራት ሲገባ ያለመኖሩ ለክፍተቱ ምክንያት ሆኗል። በዚህ ምክንያት አሁን ለአንድ ቤተ-ክርስቲያን ሙሉ ንዋየ ቅድሳት፣ ከብረት ነክ መአድናት የሚሰሩት፣ ከብረት ባለሙያ ዘንድ፣ ከእንጨት የሚሰሩት፣ ከእንጨት ባለሙያ፣ ከስንደዶና መሰል ጥሬ እቃ የሚሰሩት እንዲሁ ከሌሎች ባለሙያዎች ዘንድ የሚሰባሰቡ ናቸው። የኢ.ኦ.ተ.ቤ ይህንን የተበታተነ ቦታ ያሉ ባለሙያዎን በአንድ በማደራጀት በየዘመኑ እንደየዘመኑ ቀኖናውን ተከትለው እንዲሰሩ ተቋማትን በብዛት ብታቋቁም ከሃይማኖታዊ ጠቀሜታው ባሻገር የተለያዩ ሀገራዊ ጠቀሜታዎች ማበርከት ትችላለች። አልያም የተለያዩ የመንግስት ተቋማት እንደ አንድ ተቋም ባለሙያዎቹን ቢያደራጅ ቤተክርስቲያኗ ለሃይማኖቱ የሚሆናትን ጥሬ እቃ ታገኛለች።

ባለሙያዎቹ ደግሞ ስራቸውን በመስራት የገቢ ምንጭ፣ እውቀት ማዳበሪያ የተሻለም ፈጠራ የሚያመጡበትን አጋጣሚ ይፈጥራል።

ከቱሪዝም ጋር በተያያዘ የንዋየ ቅድሳቱን ጥበባዊ መልኮች በመጠቀም በተበታተነ መልኩ የሚሸጡትን በአንድ ተቋም በማደራጀት ቢሰራ የገቢ ምንጭ ብቻ ሳይሆን የሀገርን መልካም ገጽታ ለዓለም ማስተዋወቂያ መንገድ ነው። ለዚህም ለምሳሌ በየቦታው የተለያዩ የመስቀል አይነቶችን፣ የቅዱሳን ስእል፣ የጥንት አብያተ ክርስቲያናት ፎቶዎች ከቁሳዊ ባህሉ ጋር በማያያዝ ሀገር በቀል እውቀትን ተከትለው እንዲዘጋጁ በማድረግ ማዘጋጀት አንዱ ማሳያ ይሆናል። ሌላው ከእነዚህን ንዋየ ቅድሳት መካከል አጫጭር መግለጫዎችን በመስራት ፎቷቸውም ሆነ ጽሁፉ ቅርስ ሆኖ እውቀት ማስተላለፊያም የገቢ ምንጭም መሆን ይችላሉ። ለንዋየ ቅድሳቱ ሀገራዊ ጠቀሜታ ሲባል የትኛውም ሀገራዊ ተቋምና ዜጋ ቁሳዊ ሀብቶችን የመስራት የማዳበር የማዘመን በቅርስነት የማቆየት ሀላፊነቱን ሊወጣ ቢችል ጥሩ ይሆናል።

### ይሁንታ

ከጥናቱ በመነሳት አጥኚዋ የሚመለከታቸው አካላት ቢሰሩ ይበጃል የምትለውን ይሁንታ ሀሳብ እንደሚከተለው አቅርባለች።

**ከኢ.ኦ .ተ.ቤ የሚጠበቁ፡-**

- ✓ የኢ.ኦ.ተ.ቤ ንዋየ ቅድሳት የሚሆኑ ቁሶችን መስራት የሚችሉ ባለሙያዎን በአንድ በማደራጀት አንድ የባህል ኢንዱስትሪ ብታቋቁም፣ ለበርካታ ምእመናን የስራ መስክ ለመክፈት፣ ሀገር በቀል የእውቀት ሽግግሩ እንዳይቋረጥ እንዲያውም እንዲበለጽግ ለማድረግ ያስችላታል።
- ✓ በየአብያተ ክርስቲያናቱ እቃቤት ለዘመናት የተቀመጡና ለብልሽት እየተዳረጉ ያሉ ንዋያተ ቅድሳትን በተሻለ ቦታ የሚቀመጡበት መንገድ ቢታሰብበት፡፡
- ✓ በየአብያተ-ክርስቲያናቱ የሚገኙ ንዋያተ ቅድሳት ብዛትና አይነት እንዲሁም የተሰሩበት ጥሬ እቃና ዘመን የሚመዘገብበትን ደንብ ማዘጋጀት ቢቻል፡፡
- ✓ ከሌሎች የእውቀት ዘርፎች ጋር በተያያዘ የእያንዳንዱ ንዋያተ ቅድሳት ውክልና/ትዕምርት ከሥነ ጽሑፍ ሙያ አንጻር ቢጠና።
- ✓ በምሕንድስናው የትምህርት መስክ የኢ.ኦ.ተ.ቤ የሕንጻ ቤተ-ክርስቲያናት የአሰራር ጥበብ ቢጠና፣ባህልና ቱሪዝም ሚኒስተር ወይም መሰል ተቋማት በአብያተ-ክርስቲያናት እቃቤት የተቀመጡና አገልግሎት መስጠት ያቆሙትን ንዋያተ ቅድሳት ከኢ.ኦ.ተ.ቤ ጋር በመተባበር ሙዝየም ሊገቡ የሚችሉበትን መንገድ ቢያመቻች፣ ለንዋያተ ቅድሳቱም ሕልውና ለሀገርም ቅርስ የገቢ ምንጭም ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

## ዋቢ ጽሁፎች

ሀብተማርያም ወርቅነህ። 1963። ጥንታዊ የኢትዮጵያ ትምህርት። አዲስ አበባ ብርሃንና ሰላም
ቀዳማዊ/ሥላሴ ማተሚያ ቤት።

ሉሌ መልአኩ። 1986። የቤተክርስቲያን ታሪክ። አዲስ አበባ ትንሣኤ ማተሚያ ድርጅት።

ነጋሽ በቀለ። 1988። "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን አስተዳደርና ትምህርት አጭር
ጥናታዊ ጽሁፍ።" ያልታተመ።

አስኳል አማረ። 1994።ንዋየ ቅድሳትን ለአገልግሎት ሊያውሏቸው ይገባልን። ሐመር። አዲስ አበባ ብራና
ማተሚያ ቤት።

ዐብይ ፍትህ አወቅ። 1963። "ንዋየ ቅድሳት"። ዲማጽ (ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሁፍ ትምህርት
ክፍል አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ። 1948። መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ መዝገበ ቃላት ሐዲስ። አዲስ አበባ።
አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

ክንፈ ገብርኤል አልታዬ። 1992። ሥርዓተ ቤተ-ክርስቲያን። አዲስ አበባ። ትንሣኤ ማተሚያ ድርጅት።

ክንፈ ገብርኤልና ጌታቸው። 1998። ሥርዓተ ቤተክርስቲያን። አዲስ በባ ትንሣኤ ማተሚያ ቤት።ኢትዮጵያ

መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር።1980። መጽሐፍ ቅዱስ (የብሉይና የሀዲስ ኪዳን መጻህፍት)።
አዲስአበባ። ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ-ክርስቲያን። 1994። የኢትዮጵያ ቤተ-ክርስቲያን ትላንትና ዛሬና
ነገ። አዲስ አበባ ሜጋ ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ።

ያሬድ ገ/መድህን። 1996። ኖኅተ ሰማይ። አዲስ አበባ። ሜጋ ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ።

ፈቃደ አዘዘ። 1991። የሥነ-ቃል መምሪያ። አዲስ አበባ። ቦሌ ማተሚያ ድርጅት።

ፍሬሕይወት ባዩ። 2000። "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖትን ዋያተ ቅድሳት ሃይማኖታዊና
ፎክሎራዊ ገጽታ"ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሁፍ ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ
በኢትዮጵያ ሥነጽሁፍና ፎክሎር። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።